ግ604

# በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር
# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1988 በጀት ዓመት
## ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1988
July 1994.

<u>በኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስቴር</u>
<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን</u>

# <u>የ1988 በጀት ዓመት</u>
# <u>ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት</u>

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1988

## ማውጫ

አርዕስት ገጽ


1. መግቢያ 1

2. የሕዝብና ቤቶች ስታቲስቲክስን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት 2

2.1 የሕዝብና ቤት ቆጠራን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት 2
2.1.1 በሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኤዲትና ኮድ ማድረግን እንደዚሁም በኮምፒዩተር ውስጥ ማስገባትን (Data Entry)በሚመለከት 2
2.1.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርቶች ዝግጅትን በሚመለከት 3
2.1.3 የድኅረ ቆጠራ ጥናትን በሚመለከት 3
2.2 ሕዝብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የተከናወኑ ጥናቶችን በሚመለከት 3
2.3 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት 4

3. በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስታቲስቲክስ የተከናወኑ ተግባራት 5

3.1 ከግብርና ስታቲስቲክስ ጥናቶች በተሰበሰቡ መረጃዎች የተከናወኑ ተግባራት 5
3.2 በብሄራዊ አካውንትስ፣ በቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ጥናት በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት 9
3.3 ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በተሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት 12
4. የካርታ ሥራና ሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት 13
4.1 የካርታ ሥራን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት 13
4.2 የሰርቬይ ዲዛይን ስራን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት 14

5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሄት ዝግጅትን በሚመለከት 16

6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና 16

6.1 የሰው ኃይል ሁኔታ 16
6.2 የሰው ኃይል ሥልጠና 18
7. የበጀት አጠቃቀም 19
8. የዕቃ ግዢና በዕርዳታ የተገኙ ዕቃዎች፣ የመኪናዎች ጥገና፣ ስምሪት፣ የኢንሹራንስ አገልግሎት፣ የመጽሄቶች ሽያጭና ነፃ እደላ እና የመሳሰሉትን በሚመለከት የተከናወኑ ሥራዎች 22
9. በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች 26

# የ1988 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ሪፖርት

## 1. መ ግ ቢ ያ

ይህ ሪፖርት ከሐምሌ 1 ቀን 1987 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1988 ድረስ ያለውን የአንድ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ጊዜን ይሸፍናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ጥናታቸው ባለፈው በጀት ዓመት ተጀምሮ ባለመጠናቀቁ ወደዚህ በጀት ዓመት እንዲሸጋገሩ የተደረጉ እና በዚህ በጀት ዓመት ሊጠኑ የታቀዱ የአዳዲስ ፕሮጀክቶች ጥናት ተካሂዷል።

በ1988 በጀት ዓመት ውስጥ የተካሄዱ ጥናቶች ብዛት አሥር ሲሆኑ እነዚህም፣

1. የሕዝብና ቤት ቆጠራ የመረጃዎች ቅንብር፣
2. የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጪ ጥናት፣
3. የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት፣
4. የችርቻሮና የአምራች ዋጋ ጥናት፣
5. የግብርና ስታቲስቲክስ ጥናት፣
6. የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
7. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች ጥናት፣
8. የንግድና ትራንስፖርት መገናኛና ፋይናንስ ጥናት፣
9. የማህበራዊ ስታቲስቲክስ ጥናት፣ እና
10. የወሊድ ሁኔታ ጥናት/በአዲስ አበባ/ናቸው።

በተራ ቁጥር 2 እና 3 የተጠቀሱት ጥናቶች በ1987 ዓ.ም በበጋውና በክረምት ወራት ማለትም በጥናቶቹ ልዩ ባህሪይ ምክንያት በታህሣሥና በጥር ወራት በአንጻራዊ ሁኔታ በቂ ምግብ በሚገኝበት እና የምግብ እጥረት በሚኖርበት በሰኔና በሐምሌ ወራት ለማጥናት ታቅዶ ነበር ። ነገር ግን ሁለተኛው አገር አቀፍ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሥራ በአንዳንድ ክልሎች በታቀደው የጊዜ ገደብ ውስጥ ባለመጠናቀቁ ምክንያት በሁለተኛው ዙር መካሄድ የነበረበት የነዚህ ጥናቶች ፕሮግራም ወደ 1988 በጀት ዓመት ማሸጋሸግ በማስፈለጉ የተላለፉ ነባር ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ሌሎቹ ግን አዲስ ጥናቶች ናቸው።

በተራ ቁጥር ከ6-10 የተጠቀሱት ጥናቶች የሚካሄዱት በመደበኛ በጀት ሲሆን ቀሪዎቹ ጥናቶች ግን በካፒታል በጀት የሚከናወኑ ናቸው ።

ከላይ ለተጠቀሱት ፕሮጀክቶች የተደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በዝርዝር በሪፖርቱ ውስጥ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ ጋርም የሰው ኃይል ሁኔታና የፋይናንስ ወጪዎችን የሚያሳዩ አኃዛዊ መረጃዎች ሪፖርቱ ይዟል።

በሌላ በኩል የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የተጣለበትን የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችል በበላይ አካል ትኩረት ተሰጥቶአቸው መፍትሄ የሚሹ አጠቃላይ ችግሮች በሪፖርቱ መጨረሻ ክፍል ላይ እንዲካተቱ ተደርጎአል።

## 2. <u>የሕዝብና ቤቶች ስታቲስቲክስን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት</u>

በአሁኑ ጊዜ ከአፋርና ከሱማሌ ብሄራዊ ክልሎች በስተቀር የሌሎች ብሄራዊ ክልሎች የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች ተሰብስበው ተቀነባብረው፣ ሪፖርታቸው ተዘጋጅቶና ታትሞ ለተጠቃሚዎች በመሠራጨት ላይ ነው። ከላይ በተጠቀሱት ብሄራዊ ክልሎች የተሰበሰበው የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ግን በቆጠራው ወቅት በነበረው ችግርና በመጀመሪያ ደረጃ ውጤት (Preliminary result) መሠረት በመረጃው በታየው ችግር ምክንያት ውጤቱ ተቀባይነት ባለማግኘቱ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ማዕከላዊ ኮሚሽን ድጋሚ ቆጠራ እንዲካሄድ ወስኖአል። በመሆኑም በነዚህ ብሄራዊ ክልሎች ድጋሚ ቆጠራ ለማካሄድ የባለሥልጣኑ መሥሪያቤት የቅድመ ቆጠራ ዝግጅት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ነው።

### 2.1 <u>በሕዝብና ቤት ቆጠራን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት</u>

#### 2.1.1 <u>የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ኮድና ኤዲት ማድረግን እና በኮምፒዩተር ውስጥ ማስገባትን በሚመለከት፣</u>

ሀ. በዚህ በጀት ዓመት ኤዲትና ኮድ ለማድረግ የታቀዱት ቆጠራ ቦታዎች ኤድትና ኮድ ተደርገው ጠቅላላ ሥራው ሙሉ በሙሉ በታኀሣሥ ወር 1988 ዓ.ም መጨረሻ ተጠናቋል።

ለ. በሕዝብና ቤት ቆጠራ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በኮምፒዩተር ውስጥ ማስገባትን በሚመለከት ጠቅላላ ሥራው ሙሉ በሙሉ በየካቲት ወር 1988 መጨረሻ በኮምፒዩተር ውስጥ ገብተዋል።

ሐ. የሕዝብና ቤት ቆጠራው መረጃ ወደ ኮምፒውተር የገባላቸው የቆጠራ ቦታዎች ስትራክቸራል ኤዲትና ባክ አፕ ተከናውኖአል።

መ. የታቡሌሽን ሥራን በሚመለከት ከአፋርና ከሱማሌ ብሄራዊ ክልል መረጃዎች በስተቀር የሌሎቹ ብሄራዊ ክልሎች ሙሉ በሙሉ (93%)ተጠናቋል።

### 2.1.2 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ሪፖርቶች ዝግጅትን በሚመለከት

ሀ. የቆጠራ ሪፖርቶች ዝግጅትን በሚመለከት በዚህ ዕቅድ ጊዜ ውስጥ የዘጠኙም ብሄራዊ ክልሎች ስታቲስቲካዊ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ታትሟል። ከዘጠኙ ብሄራዊ ክልሎች መሃል የአዲስ አበባ፣ የሐረሪ፣ የትግራይ፣ የአማራ፣ የጋምቤላ እና የኦሮሚያ ሪፖርቶች ለተጠቃሚዎች በመሰራጨት ላይ ናቸው። የአዲስ አበባ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ አናሊቲካል ሪፖርት ዝግጅትም ተጀምሮአል።

ለ. የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎችን በኮምፒውተር ማረምና ሠንጠረዥ የማውጣቱ ተግባር በአዲሱ የአስተዳደር አወቃቀር መሠረት የትግራይ፣የጋምቤላ፣የኦሮሚያ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ፣ የአማራ ብሄራዊ ክልል መረጃዎች በሙሉ እንደገና የኮምፒውተር እርማትና የማባዣ ቁጥር ተሠርቷል።

ሐ. 1986/87 የቫይታል ስታቲስቲክስ ጥናት ሪፖርት ተጠናቆ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች በመሠራጨት ላይ ነው።

መ. የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤቶችን የፓፕ ማፕ(POP.MAP) ፕሮግራምን በመጠቀም በሕዝብና ቤት ቆጠራ በአትላስ(CENSUS ATLAS) መልክ በኮምፒውተር የማዘጋጀት ሥራ እየተከናወነ ነው።

### 2.1.3 የድኅረ ቆጠራ ጥናትን በሚመለከት

የ1987 የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሽፋን ደረጃንና የመረጃ ጥራትን ለመገምገም የተካሄደው የድኅረ ቆጠራ ጥናት መረጃ በስድስት ዶሚይኖችና በሀገር አቀፍ ደረጃ አስፈላጊ ሠንጠረዦች በገጠርና በከተማ በመለየት ተሠርተዋል። ሠንጠረዦቹም ከታዩ በኋላ አንዳንድ እርማቶች ተደርገዋል።

## 2.2 በአፋርና በሱማሌ ብሄራዊ ክልሎች የሚካሄደው ድጋሚ የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቅድመ ዝግጅትን በሚመለከት

በሁለቱ ብሄራዊ ክልሎች ተካሄዶ የነበረው የሕዝብና ቤት ቆጠራ በድጋሚ እንዲካሄድ በተወሰነው መሠረት አስፈላጊዎቹ የቆጠራ ቅድመ ዝግጅቶች ተካሂደዋል። ከነዚህ ውስጥ:-

- የቆጠራውን ስልት መቀየስ፥
- መጠይቆችና መመሪያዎች ማዘጋጀትና ማተም፥
- አስፈላጊውን በጀትና የሰው ኃይል መጠን ማዘጋጀት ፥
- ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ የቆጠራ ሃላፊዎች መመደብና ማሠማራት ፥
- የዘላን ገበሬ ማኅበራትና የመንደሮች ዝግጅት ለማዘጋጀት በየወረዳው ማሰማራት፥
- የአፋር ብሄራዊ ክልል ቆጠራን የሚያስፈፅሙ አሠልጣኞችን ማዘጋጀትና ማሰማራት፥
- የአፋር ብሄራዊ ክልል ቆጠራን የሚያስፈፅሙ ተቆጣጣሪዎችን መመልመልና ማጓጓዝ፥
- የአፋር ብሄራዊ ክልል ቆጠራን የሚያስፈፅሙ ቆጣሪዎችን መመልመል፥
- የአፋር ብሄራዊ ክልል ቆጠራን የሚያስፈፅሙ የስልጠና ማዕከላትን ማቋቋም እና
- የሁለተኛ ደረጃ የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት በአራተኛው ሩብ ዓመት የተከናወኑ ሥራዎች ናቸው ።

## 2.3 ሕዝብ ነክ በሆኑ ጉዳዮች የተከናወኑ ጥናቶችን በሚመለከት

በአዲስ አበባ የወሊድ ሁኔታ ጥናትን በሚመለከት የሙከራ ጥናትና ዋናው ጥናት ተከናውኖ መረጃው በኮምፒዩተር ውስጥ ገብቷል። መረጃውን ለመተንተን የሚያስፈልጉ ሠንጠረዦችም በኮምፒዩተር የወጡ ሲሆን ሪፖርቱ በመዘጋጀት ላይ ነው።

## 2.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ለሚገኙ የማኅበራዊ ስታቲስቲክስ ሠራተኞች በታኅሣሥ ወር 1988 ሊሰጥ ታስቦ ለነበረው የሙያ ሥልጠና የዶክሜንት ዝግጅት ተጠናቋል።

ለ. የጀንደር ስታቲስቲክስ /Gender Statistics/ መረጃዎችን አስመልክቶ ከተጠቃሚዎች ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢው አገልግሎት ተሰጥቷል።

ሐ. ሕዝብ ነክ በሆኑ ጉድዮች ለሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች አስፈላጊው ትብብር ተደርጓል።

መ. በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የጥናትና ምርምር ኢኒስቲትዩት ለሚማሩ የሥነ-ሕዝብ ድኅረ ምረቃ ተመራማሪዎች በ1987 ስለተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ አሠራር በተመለከተ ገለጻ ተደርጓል።

## 3. የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ስታቲስቲክስን በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ መረጃዎች ክምችት ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት በግብርና፣ በብሄራዊ አካውንትስ፣ በቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች፣ በማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ በኤሌክትሪሲቲ፣ በትራንስፖርትና መገናኛ፣ በንግድ እንቅስቃሴና በፋይናንስ ላይ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ያቀነባብራል፣ ይተነትናል እንደዚሁም የጥናቱን ውጤት ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል። በመሆኑም ከሐምሌ 1 ቀን1987 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1988 ድረስ በተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራም የታቀፉ ጥናቶችና የሌሎች መደበኛ ጥናቶች ዕቅድ አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.1 ከግብርና ስታቲስቲክስ ጥናቶች በተሰባሰቡ መረጃዎች የተከናወኑ ተግባራት።

#### 3.1.1 የሰብል ትንበያ ጥናትን በሚመለከት

ሀ. የ1988 የሰብል ትንበያ መረጃዎች ከመስክ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት እንደመጡ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ፣የቬሪፊኬሽን እና መረጃ ወደ ኮምፒዩተር የማስገባት ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ መረጃውን በኮምፒውተር በማቀነባበር ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል። እንደዚሁም የተዘጋጀው ሪፖርት ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

ለ. የቅድሚያ ሰብል ትንበያ ጥናት ለመጀመር በመስከረም 1988 ዓ.ም በሙከራ ደረጃ በአማራው ብሄራዊ ክልል መረጃ ለመሰብሰብ ሠራተኞች ወደ መስክ ተልከው መረጃው ተሰባስቦ ተቀነባብሮአል።

ሐ. የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃ አሰባሰብ ጥራት ለመከታተል የዋናው መሥሪያ ቤት ባለሙያዎች በመስክ በመገኘት የክትትልና የግምገማ ሥራ አከናውነዋል።

#### 3.1.2. የግብርና ናሙና ጥናትን በሚመለከት

ሀ. የ1988 የመኸር ወቅት ጥናት መረጃዎቹ ከመስክ ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት እንደደረሱ የኤዲቲንግና ኮዲንግ ፣ የቬሪፊኬሽን እና መረጃ ወደ ኮምፒዩተር የማስገባት ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን መረጃውን በኮምፒውተር

በማቀነባበር ሪፖርቱ ተዘጋጅቷል። እንደዚሁም የተዘጋጀው ሪፖርት ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

ለ. የ1986 እና የ1987 በበልግ ወቅት የታረሰ መሬት ስፋትና የምርት መጠን መረጃ ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።የ1988 መረጃም የማቀነባበርና የሪፖርት ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ ነው።

ሐ. ከ1972 እስከ 1986 የግል ባለይዞታዎች የመኸር ወቅት የታረሰ መሬትና የምርት መጠን ተከታታይ መረጃዎች /Time series data/ በየሴክተሩ ወደ ኮምፒዩተር የማስገባቱ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን 1987 መረጃም በየሴክተሩ ወደ ኮምፒዩተር የማስገባቱ ሥራ ተጠናቆ የመጨረሻ እርማት እየተደረገበት ነው።

መ. 1986-1988 ዓ.ም ድረስ የታረሰ የመሬት ስፋትና የምርት መጠን ለመንግሥት እርሻ ልማት ድርጅቶች ተሰብስቧል።

### 3.1.3 የእርሻ ሥራ /Agricultural practices/ መረጃን በሚመለከት

ሀ. የ1988 የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ መረጃ የማቀነባበር እና የሪፖርት ዝግጅት ሥራ ተጠናቆ ለሕትመት ዝግጁ ሆኖአል።

ለ. የ1987 የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ መረጃ ተቀነባብሮ በመጠናቀቁ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

ሐ. የ1984 የመኸር ወቅት የእርሻ ሥራ ተቀነባብሮ በመጠናቀቁ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

### 3.1.4 የመሬት አጠቃቀም /Land utilization/ መረጃን በሚመለከት

ሀ. የ1988 የመሬት አጠቃቀም መረጃ የማቀነባበሩ ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ በመዘጋጀት ላይ ነው።

ለ. የ1987 የመሬት አጠቃቀም መረጃ ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

### 3.1.5 የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ቀፎዎች መረጃን በሚመለከት

ሀ. የ1988 የቤት እንስሳት፣ ዶሮና ንብ መረጃ በመቀነባበር የሪፖርቱ ዝግጅት ተጠናቆ በመታተም ላይ ነው።

ለ. የ1987 የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ ቀፎዎች ብዛት መረጃ ተቀነባብሮና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

ሐ. የ1988 የቤት እንስሳት፣ የዶሮና የንብ መረጃ ክሮስ ታቡሌሽን /የባለይዞታዎች፣ የመሬት፣ የእንስሳት ብዛትና ዝምድና የሚያሳይ ሪፖርት/ ቅንብር ተጠናቆ የሪፖርቱ ዝግጅት በመካሄድ ላይ ነው።

መ. ከ1973 እስከ 1984 የቤት እንስሳት ተከታታይ መረጃ /Time series data/ ተጠናቆ ለሕትመት ዝግጁ ሆኗል።

ሠ. የ1985 እና የ1986 የቤት እንስሳት የመረጃ ክፍተትን ለማሟላት የትንበያ ሥራ / Projection/ ተጠናቆ ውጤቱን ለመገምገም ዝግጅት እየተደረገ ነው።

### 3.1.6 ሌሎች የተከናወኑ ሥራዎች

ሀ. ከመስከረም ወር 1988 ጀምሮ በመካሄድ ላይ ላሉት ጥናቶች የሚያገለግሉ መጠይቆችና መመሪያዎች ተዘጋጅተውና ታትመው ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተልከዋል። የመጠይቆችና የመስክ መገልገያ ዕቃዎች ጉድለት ላጋጠማቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በጊዜው ተልከዋል።

ለ. በእርጅና ምክንያት ፍጥነት በሌለው ሚይን ፍሬም ኮምፒዩተር ይቀነባበር የነበረውን የግብርና መረጃ ከUSAID በተገኘው የባለሙያ ድጋፍ በመታገዝ ወደ ፈጣኑ ፐርሰናል ኮምፒዩተር ሲስተም እንዲቀየር በመደረጉ የሰብል ትንበያ ጥናት መረጃን በአጭር ጊዜ ውስጥ አቀነባብሮ ውጤቱን ወቅታዊ ለማድረግ ተችሏል።

ሐ. በአሁኑ ወቅትም ከBureau of the Census በመጡ ባለሙያ ድጋፍ የዋናው መኸር ወቅትና ሌሎች ከግብርና የሚገኙ መረጃዎች በፐርሰናል ኮምፒዩተር ሲስተም እየተቀነባበሩ ነው።

መ. ከግብርና ናሙና ጥናት የሚገኘውን መረጃ ጥራት ከፍ ለማድረግና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴን ለማሻሻል ከUSAID ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ከUSDA የግብርና ስታቲስቲክስ አገልግሎት ሁለት ባለሙያዎች ለሁለት ሣምንታት ያህል መጥተው ሁኔታዎችን አጥንተው ተመልሰዋል።

ሠ. በቀጣይነት እነዚህ ባለሙያዎች ባቀረቡት የፕሮጀክት ፕሮፖዛል መሠረት ለአምስት ዓመታት የሚያስፈልገው የበጀት ግምትና የመምሪያውን አቅም ግንባታ ከፍ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ያካተተ ተዘጋጅቶ ለUSAID ተልኳል።

ረ. የ1987 የግብርና ጥናት ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨትና እንዲሁም የግብርና ጥናት መጠይቆችን ለማስተዋወቅ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ሌሎች ግብርና የሚመለከታቸው መ/ቤቶች መንግሥታዊ መሥሪያቤቶችና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለተውጣጡ ኤክስፐርቶች የአንድ ቀን ሴሚናር ተካሂዷል። በሴሚናሩ የተሳተፉት ኤክስፐርቶች በጥናቱ ሪፖርቶችና በጥናቱ ዶክመንቶች የመረጃ ስርጭት ያላቸውን አስተያየትና ሃሳብ በጽሁፍ እንዲሰጡ በተጠየቁት መሠረት ብዙዎቹ በጥናቱ መካተት ይኖርባቸዋል ያሉዋቸውን አስተያየት ሰጥተዋል።

ሰ. በቀጣይነት በግንቦት ወር User producer committee ተቋቁሞ ባቀረቡት ማሻሻያ ሃሳብ ላይ ተነጋግሮ በሚቀጥሉት ጥናቶች መካተት የሚገባቸውን መረጃዎች በከፊል ለይቶ ሲያወጣ ቀሪውን ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን አቅሙ በፈቀደ መጠን ለማካተትና ለመሥራት እንደሚሞክር ከኮሚቴው አባላት ጋር ሥምምነት ላይ ተደርሷል።

ሸ. ከኢትዮጵያ እንስሳት ባለሙያዎች ማኅበር በተጠየቀው መሠረት Livestock Resources and Production Statistics Experience in Central Statistical Authority በሚል ርዕስ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ ተሰጥቷል።

ቀ. የ1988 የበልግ ወቅት ግብርና ናሙና የመሬት ስፋትና የምርት መጠን ከአካባቢ መለኪያ ወደ ሜትሪክ መለኪያ መቀየር የሚያስችል Conversion factor ተዘጋጅቶ 1988 የበልግ ወቅት መረጃ በዚሁ ተሠርቷል።

በ. ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን በተጠየቀው መሠረት የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና የሳምፕሊንግ ፕሮሲጀር ማስጠንቀቂያ ሥልጠና የሚረዳ ጽሁፍ ተዘጋጅቷል።

ተ. በ1989 ሊካሄድ ለታቀደው የእንስት ጥናት በጀትና የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ተዘጋጅቷል።

ቸ. በ1989 ሊካሄድ ለታቀደው የግብርና ናሙና ጥናት ቅድመ ዝግጅት እየተጠናቀቀ ነው።

ተ. የባለሥልጣኑ መሥሪያቤት ከሚቺጋን ስቴት ዩንቨርስቲ ጋር በአደረገው ስምምነት መሠረት ለሚያካሄደው " የሰብል ገበያ ጥናት ፕሮጀክት "(Grain market project) አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበው ኤዲትና ኮድ ተደርገዋል።

ኀ. በደብዳቤና በግንባር መረጃ ለጠየቁ ድርጅቶችና ግለሰቦች ትብብር ተደርጓል።

## 3.2 <u>በብሄራዊ አካውንትስ፣ በቤተሰብ በጀትና ዋጋዎች ጥናት በተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ የተከናወኑ ሥራዎች</u>

### 3.2.1 <u>የአምራችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት</u>

ሀ. <u>የአምራችና የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በገጠር</u>

- የ1988 ከመስከረም እስከ የካቲት ያለው የዋጋዎች መረጃ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። የመጋቢትና የሚያዚያ ወራት መረጃዎች ዳታ ኢንትሪ ተጠናቆ እርማት እየተደረገ ነው።

- የ1986 እና 1987 በገጠር የአምራችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ሪፖርት ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

ለ. <u>የችርቻሮ ዋጋ ጥናት በከተሞች</u>

- የ1988 ከመስከረም እስከ የካቲት ወራት ያለው የዋጋዎች መረጃ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። የመጋቢትና የሚያዚያ ወራት መረጃዎች ዳታ ኢንትሪ ተጠናቆ እርማት እየተደረገ ነው።

- የ1985፣1986 እና የ1987 የዋጋ ስታቲስቲክስ መረጃዎች ቅንብር ተጠናቆ ሪፖርቱ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።

ሐ. <u>የዋጋ ኢንዴክስ ሥራ</u>

- የ1988 የአዲስ አበባ ከተማ የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ በየወሩ እየተዘጋጀ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨ ሲሆን የገጠሩን የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስም በየሩብ ዓመቱ እየተዘጋጀ እስከ መጋቢት 1988 ድረስ ያለው መረጃ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

- የ1986 ዓመታዊ የገጠር የችርቻሮ ዋጋ ኢንዴክስ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሠራጭቷል።
- የእንዴክሱን ፎርማት ተጠቃሚዎች በቀላሉ ሊረዱትና ሊገነዘቡ በሚያስችል መልክ ተዘጋጅተው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል።

3.2.2 <u>የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት</u>

ጥናቱ የተካሄደው በሁለት ዙር ሆኖ የመጀመሪያ ዙር ከሰኔ 4 ቀን 1987 እስከ ነሐሴ 3 ቀን 1987 በገጠር በተመረጡ 620 ቆጠራ ቦታዎች /ከእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ በተመረጡ 12 ቤተሰቦች፣ በጠቅላላው 7,440 ቤተሰቦች / እንደዚሁም በከተማ ደግሞ በተመረጡ 323 ቆጠራ ቦታዎች / ከእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ በተመረጡ 15 ቤተሰቦች በጠቅላላው 4,845 ቤተሰቦች/ ነው። በጠቅላላው በገጠርና በከተማ 12,285 ቤተሰቦች በጥናቱ ተሸፍነዋል።

ጥናቱ በሁለት ዙር የተካሄደ ሲሆን የጥናቱ ውጤትም የኅብረተሰቡን የገቢ፣ የፍጆታና ወጪ መጠን በሀገር አቀፍ ክልል፣ለ10 ትላልቅ ከተሞች ፣በተወሰኑ የክልሉ አካባቢዎች የዞን ስብስቦች (Groups of Zones) ደረጃ መረጃዎች ያስገኛል።

- በሁለት ዙር የተካሄደውን የዚህን ጥናት ውጤት በአጭር ጊዜ ውስጥ ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ነው። የጥናቱ መጀመሪያ ዙር ዳታ ክሊኒግ የተጠናቀቀ ሲሆን የሁለተኛው ዙር የእርማት ኮድ አሰጣጥ ዳታ ኢንትሪ ፣መረጃ ቅንብር ...ወዘተ ሥራዎች

ተከናውነዋል። በአሁኑ ወቅት የሁለቱን ዙር መረጃዎች በማገናኘት

የመጨረሻ የዳታ ክሊኒንግ ሥራ በመከናወን ላይ ይገኛል።

### 3.2.3 <u>የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደሕንነት ጥናት</u>

ይህ ጥናት ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን የተካሄደ ሲሆን የተካሄደውም ከቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት ጋር የሰው ኀይል፣ የማቴሪያልና የሎጅስቲክስ አቅም በማቀናጀት ነው።

ጥናቱ በገጠር በ620 ቆጠራ ቦታዎች፣ በከተማ ደግሞ በ323 ቆጠራ ቦታዎች የተካሄደ ሲሆን በገጠር 7,440 ቤተሰቦች ፣ በከተማ 4,845 ቤተሰቦች፣ በጠቅላላው 12,285 ቤተሰቦች በጥናቱ ተሸፍነዋል። የጥናቱ ውጤትም የኅብረተሰቡን የድኅነት መስመር /Poverty Line/ በምን ደረጃ ላይ እንደሆነ የሚያሳይ መረጃ ያስገኛል። የዚህ ጥናት የመጀመሪያ ዙር ውጤት ዳታ ክሊኒንግ ተጠናቆ ሪፖርት ዝግጅት ደረጃ ላይ ተደርሷል። የሁለተኛው ዙር ዳታ ክሊኒን ሥራ ደግሞ በመከናወን ላይ ይገኛል።

### 3.2.4 <u>ብሄራዊ አካውንትስ</u>

የብሄራዊ አካውንትስ ለማስላት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በተመለከተ የሚከተሉት ተግባራት ተከናውነዋል።

- የእርሻውን ሴክተር በሚመለከት ከሌሎች መ/ቤቶች ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበው ከ1983 እስከ 1987 ድረስ ላለው ጊዜ ተሠርቷል።
- የኢንዱስትሪውን ሴክተር በሚመለከት ከ1983 እስከ 1987 ላለው ጊዜ ስሌት ተጠናቆ የኤሌትሪክ ዘርፍ ስሌት በመተንተን ላይ ነው።
- የቡናና ሻይ ምርት፣የከብት ሀብት፣የደንና የውሀ ሀብት ስሌቶች 90 በመቶ ተጠናቋል።
- በአጠቃላይ በስታቲስቲክስ መረጃዎች ላይ የተመሠረተውን የተወሰኑ ሴክተሮች ስሌት በሪፖርት ለማውጣት ከሥራው ከ75 በመቶ በላይ ተከናውኖአል።

### 3.2.5 <u>ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት</u>

ሀ. የቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት እንደዚሁም የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ደኅንነት ጥናት መረጃን በኮምፒዩተር ለማጠናቀር

የሚረዳ "Edit Specification"እና " Data Dictionary" እንደዚሁም "Tabulation plan" ተዘጋጅቶ ለመረጃ ማቀነባበሪያ መምሪያ ተሰጥቷል።

ለ. የዋጋ መረጃን በ"IMPS Software" ለመተንተን የሚረዱ "Data Dictionary እና "Edit Specification" ተዘጋጅቷል። እንደዚሁም የዋጋ ጥናት መረጃ የዳታ ኢንትሪ ፎርማት መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ሐ. ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ለመጡ መረጃ ፈላጊዎች ምክርና መረጃ ተሰጥቷል።

## 3.3 ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በተሰበሰቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ላይ የተከናወኑ ተግባራት

### 3.3.1 የትላልቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ስታቲስቲክስ መረጃ ጥንቅርን በሚመለከት፣

ሀ. የ1986 የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት የመረጃ ማቀነባበሩ ሥራ ተጠናቆና ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

ለ. የ1986 የኤሌትሪክ ኢንዱስትሪዎች መረጃ ተጠናቅሮ በዓመታዊ የኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ መጽሄት ውስጥ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። የ1987 መረጃም ተሰብስቦ ለማጠናቀቅ ዝግጅት ተደርጓአል።

ሐ. የ1986 የኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ የአዲስ አበባ ከተማ የሕንፃ ስራ ፍቃድ መረጃ ተሰብስቦ በሠንጠረዥ ተዘጋጅቷል።

መ. የ1987 ዓመታዊ የኢንዱስትሪ ጥናት መረጃን ለመሰብሰብ አስፈላጊው ዝግጅት ተጠናቆ መረጃዎቹ ከመስከ ተሰብስበው ሲሆን የመረጃዎቹ የኤዲቲንግና የኮዲንግ፣ እንደዚሁም የዳታ ኢንትሪ ተግባራትም ተጠናቀው ዳታ ክሊኒንግ እየተሰራ ነው።

ሠ. ለመጀመሪያ ጊዜ ለተካሄደው የ1987 ዓ.ም የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ጥናት የመረጃ አሰባሰብ ሥራ በናሙና በተመረጡት 125 ድርጅቶች ጥናቱ ተካሂዶ በተሰበሰበው መረጃ ላይም የኤዲቲንግና የኮዲንግ

እንዲሁም የዳታ ኢንትሪ ሥራ ተጠናቋል። በተጨማሪም መረጃውን በኮምፒውተር የማቀነባበሩ ሥራ ተጠናቆ በአሁኑ ወቅት የጥናቱ ውጤት በሪፖርት ለማውጣት ጥረት እየተደረገ ነው።

### 3.3.2 <u>የውጭ ንግድ ትራንስፖርት መገናኛ ስታቲስቲክስን በሚመለከት</u>

ሀ. በሀገር አቀፍ ደረጃ የአከፋፋይ ንግድና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት በ1989 ለማካሄድ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ለጥናቱ የሚያገለግሉ መጠይቆች የመጠይቅ አሞላል መመሪያ፣ የጥናቱ ውጤት የሚሞላበት ሠንጠረዥ፣ የሸቀጥና የአገልግሎት ዝርዝር ኮድ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ የሙከራ ጥናት በሦስት ከተሞች ተካሂዷል። በሙከራ ጥናቱም 455 የአከፋፋይና የአገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ተሸፍነዋል። ከሙከራ ጥናቱም በተገኘው ጠቃሚ መረጃዎች መሠረት የዋናው ጥናት ለመጀመር ዝግጅት እየተደረገ ነው።

ለ. የውጭ ንግድ ስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ትንተና የሪፖርት ዝግጅት የተሻለና የተቀላጠፈ ለማድረግ ብሎም በኮምፒዩተር ለማቀነባበር የሚረዳ የቴክኒክና የማቴሪያል እገዛ ከምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የጋራ ገበያ ድርጅት /COMESA/ጋር የትብብር ግንኙነት ተፈጥሮአል።

ሐ. የባለሥልጣኑ መሥሪያቤት ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በአደረገው ስምምነት መሠረት በጋራ "Informal Sector" ጥናት በአገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች ለማካሄድ በሚኒስቴር መሥሪያቤቱ የቀረበውን የመነሻ ሀሳብና የመጠይቆች ይዘት በማገናዘብ ጥናቱን ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

መ. ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ስታቲስቲካዊ መረጃ ጠያቂዎች አገልግሎት ተሰጥቷል።

## 4. <u>የካርታ ሥራና ሰርቬይ ዲዛይን ዝግጅትን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት</u>

### 4.1 <u>የካርታ ሥራን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት</u>

ሀ. ከሕዝብና ቤት ቆጠራ ካርታ የመስክ ሥራ ከንውን በኋላ በሀገሪቱ የነበሩት 565 ወረዳዎች በአዲሱ አደረጃጀት ወደ 436 ወረዳዎች ዝቅ ብለዋል። ከእነዚህ 436 ወረዳዎች መሃል ደግሞ 205 ወረዳዎች በአዲስ የድንበር ይዞታ የተደራጁ በመሆናቸው በዚህ ዕቅድ ዓመት ውስጥ 124

ወረዳ ካርታዎች በአማርኛ ሊሮይ ተሠርተው ዝግጁ ሆነዋል። እንደዚሁም በለውጡ መሠረት ለገበሬ ማኀበራት፣ለከተሞች፣ ለመቆጣጠሪያ ቦታዎች፣ ለወረዳዎችና ዞኖች አዲስ ኮድ በመስጠት ተመዝግበዋል። እነዚህም በተለያዩ ቅጾች ተሞልተው በኮምፒዩተር ውስጥ ገብተዋል።

ለ. የክልልና የዞኖችን ካርታ በአነስተኛ መሥፈርት ለማዘጋጀ ካርታ ለተሠራላቸው ወረዳዎች በሙሉ ከ1:50,000 መሥፈርት ወደ 1:250,000 መሥፈርት ተዛውሮ እንደገና በ1:100,000 መስፈርት በሆነ ካርታ ተዘጋጅቷል። እንደዚሁም የኢትዮጵያ ካርታ ከክልል ሁለት በስተቀር ሌሎች ክልሎችን በወረዳ የያዘ በ1:100,000 መሥፈርት ተዘጋጅቶአል።

ሐ. ሁሉም ብሄራዊ ክልል ወረዳዎች ስፋት /በኪሎ ሜትር ስኩየር /በጥላን ሜትር ተለክቶ ተዘጋጅቶአል።

መ. የተለያዩ የወረዳ ካርታዎች እንዲሸጥላቸው ለጠየቁ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለያዩ የቆጠራ ካርታዎች ፣የወረዳ ካርታዎችና የክልል ካርታዎች ተሸጠዋል። በተጨማሪም ለብሄራዊ ከተማ ልማት እንስቲቲዩት 139፣ እና ማክሮ ኢንተርናሽናል፣134፣ በድምሩ 273 የቆጠራ ካርታዎች እስከ መግለጫቸው በነፃ ኮፒ ተደርገው ተሰጥተዋል።

## 4.2 የሰርቬይ ዲዛይ ሥራን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. በ1987 የህዝብና ቤት ቆጠራ ወቅት ለቤቶችና ለቤተሰቦች መመዝገቢያ የተዘጋጀውን ቅጽ 1ን መሠረት በማድረግ ለወደፊት ለሚጠኑ ጥናቶች ለናሙና አመራረጥ የሚያገለግል ፍሬም ተዘጋጅቷል።

ለ. ለቤተሰብ ገቢ፣ ፍጆታና ወጪ ጥናት እንደዚሁም ለኢኮኖሚና ማሕበራዊ ደህንነት ጥናት መጀመሪያ እና ሁለተኛ ዙር ጥናቶች ማባዣ ቁጥሮች /Multipliers/ ተዘጋጅተዋል። የእነዚህ ጥናቶች ኮድ ቡክም ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

ሐ. በሚቀጥለው በጀት ዓመት ለሚካሄደው የቁፋሮ ጥናት /Quarrying/ የናሙና ስልት ተዘጋጅቶ በስልቱ መሠረት ናሙናዎች ተመርጠዋል።

መ. በዚህ በጀት ዓመት ለተካሄደው የኮንስትራክሽን ጥናት የናሙና ስልት ተዘጋጅቶ በስልቱ መሠረት የናሙና መረጣ ተደርጎአል።አስፈላጊዎቹ የማባዣ ቁጥሮችም ተዘጋጅተዋል።

ሠ. በዚህ በጀት ዓመት በአዲስ አበባ ለተካሄደው የወሊድ ሁኔታ ጥናት የናሙና ስልት ተዘጋጅቶ ናሙናዎች ተመርጠው ሥራ ላይ ውለዋል። የጥናቱ የማባዣ ቁጥሮች የዝግጅት ሥራም ተጠናቋል።

ረ. በ1989 በጀት ዓመት ሊጠና ለታቀደው የአከፋፋይ ንግድና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥናት ለሙከራ ጥናት የሚያገለግል የናሙና ስልት ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል። ለዋናው ጥናትም የሚያገለግል የናሙና ስልት የማዘጋጀት ሥራ እየተካሄደ ነው።

ሰ. ለ1988 የግብርና ትንበያ ጥናት ማባዣ ቁጥር ተዘጋጅቷል። ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት መለኪያ Standard Errors እና Coefficient of Variation ለተመረጡ ባህሪያት ተሰልተው ከጥናቱ ውጤት ጋር ታትመው ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

ሸ. ለ1988 የግብርና ናሙና ጥናት ለኮዲንግና ኤዲቲንግ የሚያገለግል ኮድ ቡክ ተዘጋጅቷል። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ማባዣ ቁጥሮችም ተዘጋጅተው በሥራ ላይ ውለዋል።

ቀ. በሕዝብና ቤት ቆጠራ በናሙና/ረዥም መጠይቅ / ለተሰበሰቡ ባህርያት የውጤቱ አስተማማኝነት መለኪያ ለትግራይ፣ለጋምቤላ፣ለሐረሬ፣ለአዲስ አበባ፣ ለአማራ ክልሎችና ለድሬደዋ ጊዜያዊ አስተዳደር ተሠርቷል።

በ. መሥሪያ ቤቱ ከተሃድሶ ድርጅት በጋራ ላካሄደው "የአካል ጉዳተኞች ጥናት " ማባዣዎች ተሠርተዋል። ለጥናቱ ውጤት አስተማማኝነት መለኪያ Standard Errors, Coefficient of Variation, Confidence Intervals እና Design Effect በናሙና ለተመረጡ ባህሪያት ተሰልተው ከጥናቱ ውጤት ጋር ወጥተዋል።

ተ. ለበርካታ መንግሥታዊ፣ ዓለም አቀፍና የግል ድርጅቶች መረጃ ከመስጠቱም በላይ ስለሰርቬይ ሜቴዶሎጂ ሙያዊ ምክር ተሰጥቷል።

## 5. ዓመታዊ የስታቲስቲክስ መጽሄት ዝግጅትን በሚመለከት፣

የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዐቅዶችን ለማዘጋጀት ትክክለኛና አስተማማኝ የስታቲስቲክስ መረጃዎችን መሰብሰብ ማጠናቀር፣ መገምገም፣ መተንተንና ሥርዓት ባለው መንገድ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለዚህ ዓላማ ተፈጻሚነት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ከ1959 ጀምሮ ባለማቋረጥ የሀገሪቱን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚገልጽ የስታቲስቲክስ መጽሄት አዘጋጅቷል።

ታወዩን 21ኛውን የስታቲስቲክስ መጽሄት በማተም ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት በሚመለከታቸው መምሪያዎች የመረጃዎች ቅንብር ሥራ ተጠናቋል ። በመሆኑም በመታተም ላይ ባለው መጽሄት የሚቀርቡት በርካታ ልዩ ልዩ መረጃዎች ከአያሌ ምንጮች የተገኙ በመሆናቸው ለፖሊሲና ለልማት ፕሮግራም ዝግጅትና ግምገማ ብሎም ለምርምር ተግባሮች በመነሻነት እንደሚያገለግሉ ይታመናል።

## 6. የሰው ኃይል ሁኔታና ሥልጠና

### 6.1 የሰው ኀይል ሁኔታ

በ1988 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት 470 ቋሚና 1,685 የኮንትራት በጠቅላላው 2,155 ሠራተኞች ነበሩ። በአንጻሩ 1 ሠራተኛ በዝውውር ፣10 ሠራተኞች በራሳቸው ፍቃድ፣ 9 ሠራተኛ በጡረታ እና 12 ሠራተኞች ደግሞ በሞት ምክንያት ከመሥሪያ ቤቱ ቋሚ የሰው ኃይል ላይ ሲቀነሱ 572 የኮንትራት ሠራተኞች ደግሞ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ሲካሄዱ የነበሩ ሥራዎች በመጠናቀቃቸው ከሥራ ተሰናብተዋል። በሌላ በኩል ለተለያዩ ጥናቶች ደግሞ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 20 ሠራተኞች ተቀጥረው ነበር። በመሆኑም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ያለው የሰው ኃይል ብዛት 1,571 ሲሆን ከነዚህ መካከል 438ቱ ብቻ ቋሚ ሠራተኞች ሲሆኑ 1133ቱ ደግሞ የኮንትራት ሠራተኞች ናቸው። ጠቅላላ የሰው ኃይል ብዛት በሰንጠረዥ 1 ላይ ሰፍሮአል።

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን የሰው ኃይል ሁኔታ

ሠንጠረዥ 1

| ተራ ቁ. | አጠቃላይ ሁኔታ | የሠራተኛ ቅጥር ሁኔታ | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቋሚ | ኮንትራት | ድምር |
| 1 | በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ የነበሩ | 470 | 1,685 | 2,155 |
| 2 | አዲስ ቅጥር | - | 20 | 20 |
| 3 | በዝውውር የገቡ | - | - | - |
| 4 | ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት የተዛወሩ | /1/ | - | /1/ |
| 5 | በጡረታ የተገለሉ | /9/ | - | /9/ |
| 6 | በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሥራ የተገለሉ | /22/ | /572/ | /594/ |
| | በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የነበሩ | 438 | 1,133 | 1,571 |

የቋሚ ሠራተኞች ብዛት በሙያ ሲተነተን 127 ባለሙያዎች፣ 158 መለስተኛ ባለሙያዎች፣ 153 የአስተዳደር፣ የጽሕፈትና የጠቅላላ አገልግሎት ሠራተኞች ናቸው። እንደዚሁም እነዚህ ሠራተኞች በፆታ ሲለይ 325 ወንዶች /74.0 በመቶ/ ሲሆኑ 113 ደግሞ ሴቶች /26.0 በመቶ/ ናቸው።

## 6.2 የሰው ኃይል ሥልጠና

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች በፕሮጀክት ዝግጅት፣ በመረጃ አሰባሰብ፣ በመረጃ ቅንብር፣ በመረጃ ትንተናና፣ በሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ያላችውን እውቀት ከፍ በማድረግ የሥራ ብቃታቸውን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት በዚህ ዕቅድ ዓመት ውስጥ የሰው ኃይል ሥልጠናን በሚመለከት:-

ሀ. በዚህ ዓመት ለተካሄደው ግብርና ናሙና ጥናት በአሰልጣኝነት ለተመደቡ ባለሙያዎች፣ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊዎችና ረዳቶቻቸው በዋናው መሥሪያ ቤት ውስጥ ከነሐሴ 15 ቀን 1987 እስከ ነሐሴ 22 ቀን 1987 ድረስ የ8 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል።

ለ. በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የግብርና ናሙና ጥናት ላካሄዱ መረጃ ሰብሳቢዎች ከነሐሴ 27 ቀን 1987 እስከ ጳጉሜ 6 ቀን 1987 ድረስ የ10 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሐ. በአፋር ብሄራዊ ክልል ለሚካሄደው ድጋሚ የሕዝብና ቤት ቆጠራ የአሠልጣኞች ሥልጠና በዋናው መሥሪያ ቤት በሰኔ ወር 1988 ዓ.ም ተካሂዷል።

መ. አንድ ሠራተኛ በሥነ-ሕዝብ ትምህርት ላይ ሁለተኛ ዲግሪውን ማግኘት የሚያስችል እውቀት ለማግኘት ወደ ጋና ተልኳል። እንዲሁም ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ነው።

ሠ. የ1987 የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ጥናት ለማካሄድ ለመረጃ ሰብሳቢዎች ፣ለተቆጣጣሪዎችና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተወካዮች የ7 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል።

ረ. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣንና የተሐድሶ ድርጅት በጋራ ላካሄዱት ለአካል ጉዳተኞች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናት መጠይቆችና ቅጾች ፣መመሪያዎች ፣ሠንጠረዦች በማዘጋጀት የአሰልጣኞች ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሰ. የ1987 የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ጥናት ለማካሄድ ለመረጃ ሰብሳቢዎች፣ለተቆጣጣሪዎችና ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች የ7 ቀናት ሥልጠና ተሰጥቷል።

ሸ. ለአደጋ መከላከያና ዝግጁነት ኮሚሽን ሠራተኞች በሚያዚያና በግንቦት ወራት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስልጠና ተሰጥቷል።

ቀ. በምግብ ዋስትና ጥናት ለሚሳተፉ የባለሥልጣኑ መሥሪያቤት ሠራተኞች መረጃ አሰባሰቡን በሚመለከት በሰኔ ወር ሥልጠና ተሰጥቷል።

## 7. የበጀት አጠቃቀም

ለ1988 በጀት ዓመት ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብር 12,128,668.00 የተፈቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ብር 3,880,868.00 ፥ ለካፒታል በጀት ደግሞ ብር 8,247,800.00 የተፈቀደ ነው።

ለ1988 በጀት ዓመት ለደመወዝ የተፈቀደው ብር 3,247,400 ወጪውን ሊሸፍን ባለመቻሉ በልዩነት ብር 104,568 ተጨማሪ በጀት ተጠይቆ በመፈቀዱ በጀቱ ብር 3,351,968 ሆኖ ተስተካክሏል። በመሆኑም መደበኛ በጀቱ ከብር 3,776,400.00 ወደ ብር 3,880,868.00 አድጓል።

ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደው መደበኛ በጀት በሚከተሉት የወጪ አርዕስቶች የተከፋፈለ ነው።

ለደመወዝ ................. ብር 3,351,968
ለውሎ አበል................ ብር 20,000
ለሥራ ማስኬጃ............ ብር 508,900
የተያዘ ነው።

ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው መደበኛ በጀት ውስጥ በሥራ ላይ የዋለው እንደሚከተለው ቀርቧል።

- ለደመወዝ ክፍያ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 3,265,609.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ይኸው ገንዘብ በሙሉ ነው። በመሆኑም የዕቅድ አፈጻጸሙ 100% ሆኖአል።

## የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ1988 በጀት ዓመት

### በጀት አጠቃቀም

ሠንጠረዥ ፬

| ተ.ቁ. | | ለ1988 በጀት ዓመት በመንግሥት ገንዘብ ቤት የተፈቀደ | ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ተከፋፍሎ በእ፲ ገቢ የሆነ | በሐምሌ ከገቢው ገንዘብ ውስጥ በሥራ ላይ የዋለ መጠን | ልዩነት (ቢ03 እና ቢ04) |
|---|---|---|---|---|---|
| 0 | 01 | 02 | 03 | 04 | 05 |
| 1 | መደበኛ በጀት | 3,880,868.00 | 3,680,916.00 | 3,675,333.71 | 5,582.29 |
| 1.1 | ለደመወዝ | 3,351,968.00 | 3,265,609.00 | 3,265,609.00 | — |
| 1.2 | ለአበል ክፍያ | 20,000.00 | 20,000.00 | 19,273.70 | 726.30 |
| 1.3 | ለሥራ ማስኬጃ | 508,900.00 | 395,307.00 | 390,551.01 | 4,855.99 |
| 2 | ካፒታል በጀት | 8,247,800.00 | 8,247,800.00 | 8,179,567.00 | 68,233.00 |
| 2.1 | ለብሔራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ ቀመር | 495,000.00 | 495,000.00 | 494,999.00 | 1.00 |
| 2.2 | ለብሔራዊ የተቀናጀ ቤር ኮምፒውተር ጥናት | 7,752,800.00 | 7,752,800.00 | 7,684,568.00 | 68,232.00 |
| | ጠቅላላ ድምር | 12,128,668.00 | 11,928,716.00 | 11,854,900.71 | 73,815.29 |

- ለውሉ አበል ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው በዕቅድ የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 19,273.70 /96.4 በመቶ/ነው።

- ለሥራ ማስኬጃ ከተፈቀደው በጀት ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 395,307.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 390,551.01 /98.8 በመቶ/ ነው።ለሥራ ማስኬጃ ከፍያ ወጪ የሆነው ገንዘብ ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር 76.7 በመቶ ነው።

በአጠቃላይ ከሐምሌ 1 ቀን 1987 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1988 ድረስ ወጪ የሆነው ብር 3,675,333.71 ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው መደበኛ በጀት ብር 3,880,868.00 ጋር ሲነፃፀር 94.7 በመቶ ሆኖአል።

ለባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ለ1988 በጀት ዓመት የተፈቀደው ካፒታል በጀት ብር 8,247,800. ሲሆን በሥራ ላይ የዋለው ደግሞ የሚከተለው ነው።

- ለብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች ቅንብር ሥራ ከተፈቀደው በጀት ዉስጥ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ገንዘብ በዕቅድ የተያዘው በሙሉ ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 494,999.00 ነው።

- ለብሄራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፐሮግራም ማስፈፀሚያ ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጠይቆ በእጅ ገቢ የሆነው ብር 7,752,800.00 ሲሆን ወጪ የተደረገው ደግሞ ብር 7,684,568.00 ነው። በዚህ በጀት ለብሄራዊ የተቀናጀ ሰርቬይ ፐሮግራም ማስፈፀሚያ ወጪ የሆነው ገንዘብ ለበጀት ዓመቱ ከተመደበው ጋር ሲነፃፀር አሁንም 99.1 በመቶ ሆኖአል።

በመሆኑም ከሐምሌ 1 ቀን 1987 እስከ ሰኔ 30 ቀን 1988 ድረስ ወጪ የሆነው ብር 8,179,567.00 ለበጀት ዓመቱ ከተፈቀደው ካፒታል በጀት ብር 8,247,800.00 ጋር ሲነጻጸር 99.2 በመቶ ሆኖአል።

በሌላ በኩል ለብሄራዊ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃዎች ቅንብር ሥራ መንግሥት ከመደበው ካፒታል በጀት በተጨማሪ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከዩ.ኤን.ኤፍ.ፒ.ኤ ብር 395,000.00 የገንዘብ ድጋፍ ተገኝቶ ብር 394,767.00 ለልዩ ልዩ ሥራ ወጪ ሆኖአል። ከዚህ በተጨማሪ የግብርና ሚኒስቴር ለግብርና ቆጠራ ቅድመ ዝግጅት ሥራ ብር 207,550.00 የመጀመሪያ ደረጃ ከፍያ ፈጽሞ ለጥናቱ ብር196,365 ወጪ ሆኖአል።

እንደዚሁም የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ከተሐድሶ ድርጅት ጋር በጋራ ላካሄደው የአካል ጉዳተኞች ጥናት ማስፈፀሚያ ብር 151,997.00 ገቢ ሆኖ ሥራው ተከናውኖአል። ከዚህ ሌላ ከሚቺጋን ስቴት ዩንቨርስቲ ጋር በተደረሰው ስምምነት መሠረት የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የምግብ ዋስትና ጥናት ማካሄጃ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ብር 262,651 ገቢ ሆኖ ገንዘቡ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ውሏል።

## 8. <u>የዕቃ ግዢና በዕርዳታ የተገኙ፣ የመኪናዎች ጥገናና ስምሪት፣ የኢንሹራንስ አገልግሎት፣ የመፅሄቶች ሽያጭና ነፃ ዕደላ እና የመሳሰሉትን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት።</u>

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ድጋፍ ሰጪ ክፍሎች በበጀት ዓመት ውስጥ የሚካሄዱት ጥናቶች በተያዘላቸው እቅድ መሠረት እንዲከናወኑ ብሎም የመሥሪያ ቤቱን አቅም ለማሳደግና ዕለት በዕለት የሚከናወኑ ሥራዎች የተቀላጠፉ እንዲሆኑ ዕገዛ የሚያደርጉ ሥራዎችን ያከናውናሉ።

### 8.1 <u>ዕቃ ግዢንና በዕርዳታ የተገኙ ዕቃዎችን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት</u>

#### 8.1.1 <u>የዕቃዎች ግዢ</u>

- ለዋናው መሥሪያ ቤትና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አገልግሎት የሚውሉ ብር 1,560,037.71 ወጪ በማድረግ የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ግዢ የተፈጸመ ሲሆን ዝርዝሩ በተከታዩ ሠንጠረዥ ላይ ተመልክቷል ።

**ለዋናው መሥሪያ ቤትና ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በ1988 በጀት ዓመት ለነዳጅና ለልዩ ልዩ ዕቃዎች ግዢ የዋለ ገንዘብ መጠን**

ሠንጠረዥ 3

| ተራ ቁ. | የዕቃው ዓይነት | ወጪ |
|---|---|---|
| 1 | ለነዳጅ | 606,171.82 |
| 2 | ዘይትና ቅባት | 8,264.12 |
| 3 | ለጽሕፈት መሣሪያ | 240,551.83 |
| 4 | ለመኪና መለዋወጫ | 554,238.92 |
| 5 | ለማሽን ለቢሮ መገልገያ ዕቃዎች፣ለሕንፃ መሣሪያዎችና መለዋወጫ | 75,349.35 |
| 6 | ለጽዳት ዕቃዎች | 4,326.45 |
| 7 | ሌሎች /የደንብ ልብስ፣ካርቶን፣ገመድ... ወዘተ | 71,132.22 |
| | ድ ም ር | 1,560,037.71 |

8.1.2 በዕርዳታ የተገኙ ዕቃዎች

በ1988 በጀት ዓመት የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ከገዛቸው ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በተጨማሪ ከውጭ ሀገር በዕርዳታ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ተገኝተው ገቢ ሆነዋል። ገቢ የሆኑት ዕቃዎች ዓይነትና ብዛት በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ ሠፍረዋል።

በ1988 በጀት ዓመት በዕርዳታ የተገኙ ዕቃዎች ዓይነትና መጠን

ሠንጠረዥ 4

| ተራ ቁ. | የዕቃዎች ዓይነት | ብዛት | እርዳታ ሰጪ ድርጅቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ፐርሰናል ኮምፒውተሮች | 17 | UNFPA |
| 2 | የመጠረዣ መሣሪያ | 1 | UNFPA |
| 3 | የችርቻሮ ሚዛን | 1000 | UNICEF |
| 4 | የሕትመት ወረቀት (በፓሌት) | 252 | UNFPA |
| 5 | ጌስትነር ኮፒ ፕሪንተር ከነመለዋወጫው | 1 | UNFPA |
| 6 | የኮምፒውተር ኪቦርድ | 100 | UNFPA |
| 7 | የኮምፒውተር ከለር ሞኒተር | 14 | UNFPA |
| 8 | የዜሮክስ ወረቀት (በፓሌት) | 5 | UNFPA |
| 9 | የርዝመት መለኪያ ሜትር | 1000 | UNICEF |
| 10 | ኒሳን ፓትሮል መኪና | 1 | UNICEF |
| 11 | የሂሳብ ማሽኖች | 55 | UNICEF |
| 12 | ፐርሰናል ኮምፒውተር | 1 | COMESA |
| 13 | ፕሪንተር | 2 | COMESA |
| 14 | ፐርሰናል ኮምፒውተር | 4 | USAID |
| 15 | ፕሪንተር | 2 | USAID |

በሌላ በኩል ከውጭ ሀገር በዕርዳታ የተገኙትን ልዩ ልዩ ዕቃዎች ከአሰብ ወደብ ወደ አዲስ አበባ ለማስመጣት እንደዚሁም ከጉምሩክ ለማውጣት ለመጋዘን ኪራይ ለአገልግሎት እና ለመጓጓዣ ብር 168,215.25 ወጪ ሆኖአል።

8.2 የመኪናዎች ሥምሪትና ጥገናን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. በዋናው መሥሪያ ቤት ተመድበው አገልግሎት ከሚሰጡት 21 መኪናዎች በተጨማሪ በየክልል መስተዳድሩ ለሚካሄዱ ጥናቶች 76 የተለያዩ የመስክ መኪናዎች ተመድበው አገልግሎት እየሰጡ ናቸው።

ለ. በዋናው መሥሪያ ቤት ደረጃ በጋራዥ ለተጠገኑ መኪናዎች ብር 708,152.72 እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደረጃ ለተጠገኑ መኪናዎች ደግሞ ብር177,657.97 በድምሩ ብር 885,810.69 ወጪ ሆኖአል።

## 8.3 የኢንሹራንስ አገልግሎትን በሚመለከት የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለመሥሪያ ቤቱ አገልግሎት መስጠት ላይ ባሉ 20 መኪናዎች ላይ አነስተኛና ከባድ አደጋ ደርሶ ለሁሉም መኪናዎች በመድኀን አገልግሎት አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸዋል። በሌላ በኩል የመሥሪያ ቤታችን ንብረት የሆነ ተሽከርካሪ በሦስተኛ ወገን ላይ በአደረሰው አደጋ ምክንያት ከኢንሹራንስ ጋር ባለው ውል መሠረት ኢንሹራንስ ከሚከፍለው ጣሪያ በላይ ያለውን ብር 28,217.91 መ/ቤቱ ከፍያ ፈጽሟል።

ለ. በ1988 መሥሪያ ቤቱ የመድኀን ዋስትና ለገባላቸው 97 ተሽከርካሪዎች የሚከፍለው ብር 148,208.36 ሲሆን ድርጅቱ ለባለሥልጣኑ መ/ቤት በክሬዲት ኖት ተመላሽ የሚያደርገው ብር 20,782.64 በመኖሩ ይኸው ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጎ ብር 127,425.72 ለድርጅቱ ተከፍሏል።

## 8.4 ሌሎች የተከናወኑ ተግባራት

ሀ. ከተለያዩ የቆጠራ ካርታዎች ፣የወረዳ ካርታዎችና የክልል ካርታዎች ሽያጭ ብር 43,936 ገቢ ተገኝቷል።

ለ. የሕትመት አገልግሎትን በሚመለከት በበጀት ዓመቱ ውስጥ በርካታ የሕትመት፣የጥረዛ፣የፎቶ ኮፒ እና ካርታዎች በብሉ ፕሪንት የማተም ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያህል:-

- 8500 የሕዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መጽሄቶችና እና 4500 ጥራዞች ፣
- ለልዩ ልዩ ጥናቶች አገልግሎት የዋሉ 50,800 ጥራዞችና 7660 መጽሄቶች ፣
- ለልዩ ልዩ ጥናቶች አገልግሎት የዋሉ 755,120 ቅጠል መጠይቆች እና 838 ካርታዎች ታትመዋል።

ሐ. የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በየጊዜው የሚያወጣቸውን ልዩ ልዩ ሪፖርቶች በነጻ እደላና በሽያጭ መልክ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ያሰራጫል። በመሆኑም በዚህ በጀት ዓመት 6,310 መጽሄቶች በነጻ ፥2,205 መጽሄቶች ደግሞ በብር 30,725.45,በመሸጥ ለመረጃ ተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል።

መ. በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የጥገና ሠራተኞች ከሚደረገው የጥገና ሥራ በተጨማሪ ለቢሮ እድሳትና ለልዩ ልዩ ዕቃዎች ጥገና ብር 36,933.92 ወጪ ተደርጓል።

9. <u>በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች</u>

የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት በዚህ በጀት ዓመት የሚያካሂዳቸው ጥናቶች ውስብስብና መጠነ ሰፊ እንደዚሁም ብዛት ያለው የሰው ኃይል የሚሳተፉበትና በቂ የመኪና አቅርቦትን የሚጠይቁ በመሆናቸው እንደዚሁም የሕዝብ ቆጠራ ውጤቱን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ አጠናቅሮ ለማውጣት አንዳንድ ችግሮች አጋጥመዋል። ከእነዚህም መካከል፡-

ሀ - በአብዛኛው ክልሎች የወረዳዎች መታጠፍና የዞኖች መሸጋሸግ በመደረጉ አልቆ የነበረው የመረጃዎች ቅንብር ሥራ እንደገና እንደአዲስ ሥራው በአዲሱ አወቃቀር መሠረት እንዲካሄድ በመደረጉ መሥሪያ ቤቱን ለተጨማሪ ሥራና ወጪ ከመዳረጉም በላይ ለሥራው መጓተት ምክንያት ሆኖአል።

ለ - የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ከሚጠቀምባቸው የመስክ መኪናዎች መሃል አብዛኛዎቹ የአገልግሎት ዕድሜአቸውን የጨረሱ በመሆናቸው በየጊዜው እየተበላሹ ጋራዥ ስለሚገቡ በሥራ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ችግር ተፈጥሮ ነበር። በመሆኑም በዚህ በጀት ዓመት ሊጠኑ በታቀዱ ሀገር አቀፍ ጥናቶች መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ብቃት ያለው የመስክ ቁጥጥር በማድረግ ረገድ ችግር ስላጋጠመ መንግሥት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ወደፊት ያቀዳቸውን ጥናቶች በማካሄድ ረገድ ያጋጠመውን የመኪና እጥረት ትኩረት ሰጥቶት ከወዲሁ በእርዳታ ወይም በግዢ ተጨማሪ የመስክ መኪናዎች የሚገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች እንጠይቃለን።

ሐ - በእርጅና ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑትን መኪናዎች በጨረታ ሽያጭ ለማስወገድ ተሞክሮ ከቀረጥ ነጻ ሆነው በእርዳታ የገቡ ስለሆነ ገዢ ባለማግኘታቸው የመ/ቤቱን ቅጥር ግቢ በማጣበብ ቆመው ይገኛሉ። በመሆኑም የቀረጥ ክፍያ የማይመለከታቸው ሆነው እንዲሸጡ እንዲፈቀድ ለሚመለከተው ጥያቄ ስላቀረበ የበላይ አካል ድጋፍና መመሪያ እንዲሰጥበት እንጠይቃለን።

መ- ከኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት መቋቋም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የድርጅታዊ መዋቅር ለውጥ መ/ቤታችንን አስመልክቶ የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ባለመኖሩ እንደዚሁም በመንግሥት መመሪያ የመዋቅር ለውጥ ባልተደረገባቸው መ/ቤቶች ቅጥርና የደረጃ እድገት በመታገዱ አስተዳደራዊና ቴክኒካዊ ችግሮች ተፈጥረዋል። ይህም ባሉት ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኞችን በቅጥርና በደረጃ ዕድገት መመደብ ባለመቻሉ በአፈፃፀም ላይ ችግር አስከትሏል። ስለሆነም በመ/ቤቱ ብዙ ልምድ ያካባቱ ባለሙያዎች
በየጊዜው መ/ቤቱን ለቀው እየሄዱ በመሆናቸው የባሰ ችግር ከመፈጠሩ በፊት ድርጅታዊ መዋቅሩ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ፀድቆ የሚመጣበት ሁኔታ እንዲመቻች እንጠይቃለን።